# እነ ወ/ሮ ብርቱካን ሚዴቅሳ የፈጠሩት አንጃ ለፕሮፓጋንዳ ሥራ ከፍተኛ ወጪ መድቧል፤ ብርሃኑ ነጋ የዴሞክራሲና አምባገናዊ ሥርዓት ልዩነት ማወቅ ተሥኖታል።

(ከመንግሥቴ ዓለሙ - ካናዳ)

ከቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ የተገለሉት ወይዘሮ ብርቱካንና ግብረ አበሮቿ ያቋቋሙት አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ በመባል የሚታወቀው ፓርቲ ሰኔ 7 ቀን 2000 ዓ ም ለሚያደርገው “ጠቅላላ ጉባዔ” ቅንጅትን ለማፍረስ ከቆረጡ ኃይሎች ከፍተኛ የገንዘብና የቁሳቁስ ዕርዳታ እየተደረገለት ነው።

የጠቅላላ ጉባዔውን ሂደት በተለይም ሰሜን አሜሪካና አውሮፓ ለሚገኙ የአንጃው ደጋፊዎች በሬዲዮ፡ በፓልቶክና በቴሌቪዝን ለማስተላለፍ የሚደረገው ዝግጅት ተጠናቋል።

**የኢትዮጵያ ሕዝብ በኑሮ ውድነት በሚሰቃይበትና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወገኖች ነዋሪዎች ለረሀብ አደጋ በተጋለጡበት በአሁኑ ወቅት የሕዝብን ትግል ለመናድ ጎንበስ ቀና ለሚል የአንጃ ቡድን ፕሮፓጋንዳ በመቶ ሺህ ዶላር የሚቆጠር ወጪ ማውጣት ለምን አስፈለገ?**

አንጃው ዋናውን ገቢ የሚያገኘው በተዘዋዋሪ መንገድ ከወያኔ በሚደረግለት የገንዘብ ድጎማ ቢሆንም አስቀድሞ በብርሃኑ ነጋ መሪነት በአንዳርጋቸው ጽጌና ብርሀነ መዋ ጭቃሹምነት በየከተማው በቅንጅት ሥም የተደራጁ ጭፍራዎች የሚያደርጉትን የገንዘብ አስተዋፅኦ እንዲቀጥሉ ለማበረታታትና እንዲሁም ሥራ እየሰራን ነን በማለት በባንዳነታቸው የተበላሸ ሥማቸውን ለማሳመር የታቀደ የቱልቱላ ሥራ ነው።

<u>ወያኔ ለአንጃውና ለጭፍራዎቹ ለምን ገንዘብ ያወጣል?</u>

ሕዝቡ ተባብሮ በመነሳት ወያኔ ላይ ያፋፋመውን ትግል እንዳይገፋበት ክፍፍል በመፍጠር እንዲቀዘቅዝና ተስፋ ሕዝቡም ተስፋ እንዲቆርጥ በማድረግ ለወያኔ ትልቅ ዕፎይታ ሰጥተውታል። ትግሉ ከወያኔ ጋር መሆኑ ቀርቶ እርስ በእርስ መነታረክ እስዲሰፍን አድርገዋል፤ ቅንጅትን ለማዳከም ወያኔ ያልቻለውን አንጃውና ጭፍራዎቹ ሞክረዋል፤ የወያኔ ሰላዮች በየኮሚኒቲው ገብተው ሊያከናውኑ ያልቻሉትን የመከፋፈል ሥራ የአንጃው ካድሬዎች አከናውነዋል። በየዕለቱ በሚነዙት ውዥንብር ብዙዎችን ማወናበድ ችለዋል፤ ስለዚህ አንጃውና ጭፍራዎቹ በድርጅትነት መቆየት ለወያኔ ዕድሜ መራዘም ቀጥተኛ ጠቀሜታ ስላለው ለዚሁ ሥራ የተመደቡ የወያኔ ሰዎች በየድርጅቱ አባል ለተለጣፊድርጅቶች ሥራ ማከናወኛ ጠቀም ያለ የአባልነት መዋጮ ስጦታ እየሰጡ ናቸው።

አንጃው ለህልውናው መሠረት አድርጎና ተማምኖ የተነሳው ከሕዝብ የሚያገኘውን ድጋፍ ሳይሆን የመዋሸት፣የፕሮፖጋንዳና የማወናበድ ችሎታውን ነው። ስለዚህ በፓልቶክ፡ በሬዲዮና ኢትዮጵያን የሚመዘብሩ ግለሰቦች ባለቤት በሆኑበት ቴሌቪዝን ስብሰባውን ማስተላለፋቸው የፕሮፓጋንዳና የማወናበድ ዕቅዳቸው አንዱ ክፍል ነው።

የጠቅላላ ጉባዔው ተሰብሳቢዎች ከአማራ ክልል ከኦሮሚያ ክልል ከአዲስ አበባ ወዘተ የሚባለው እነ ብርቱካን በሚያገኙት የገንዘብ ኃይል የገዟቸው እንጂ የየትኛውም ወረዳ ሕዝብ ያልመረጣቸውና የማይወክሉ በጥቅም የተገዙ ግለሰቦች መሆናቸውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንቅቆ ያውቃል።

በውጭ አገር የሚገኙ የአንጃው ደጋፊዎች የሚወዷቸው መሪዎቻቸው ከቅንጅት የተወገዱ መሆኑን ቢያውቁም በቅንጅት ሥም መጠቀማቸውን ቀጥለዋል። ለምን?

አፈንጋጮቹ ምንም ያህል መልካቸውን ለማሳመር ቢሞክሩም የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያውቃቸው በፈፀሙት ክህደትና በባንዳነታቸው ነው። በነዚህ ግለሰቦችና በመሠረቱት ፓርቲ ሥም ገንዘብ

ለመሰብሰብ ተቸግረዋል፡፡ ስለዚህ ገንዘብ ከሕዝብ ለመሰብሰብና ለማወናበድ ለጊዜው የተገኘው ዓይነተኛ መንገድ የቅንጅትን ሥምና አርማ መጠቀም ነው፡፡

ተዋራጁ (the disgraced) ብርሃኑ ነጋ በጦር ኃይል ነጻ ላወጣችሁ ነው እያለ እስካሁን የሚያወናብደው ከቅንጅት ባገኘው ሥምና በቅንጅት ሥም በሚንቀሳቀሱ ጀሌዎች አማካይነት ነው፡፡ ለንደን ላይ የብርሃኑን ስብሰባ በመቃም ሰላማዊ ሰልፍ ሊያደርጉበት ከተነሱበት ኢትዮጵያውያን በመደበቅ ጥቂት ቦዘኔዎችን ጠርቶ ያደረገው ስብሰባ ዓይነተኛ ማስረጃ ነው፡፡ ቶሮንቶ ካደረገው ስብሰባ በኋላ በሄደበት ከተማ ሁሉ ሰላማዊ ሰልፈኞችን መሸሽ ጀምሯል፡፡

በለንደኑ ስብሰባ ላይ ባሰማው የተለመደው ድንፋታ፡ ጉራና ስድብ የተሞላበት ንግግር ቱልቱላ የሚነዛበት ጎርናና ድምጹ እስኪቀጥንና የጨረባ ጩኸት እስኪመስል ድረስ በንዴት የቅንጅትን ፕሬዚዴንት ተሳድቧል፡፡ ለዴሞክራሲ እንደሚታግል ገልጾ የትግሬ ዲክታተሩን መለስ ዜናዊን አውርደን የአማራውን ዲክታተር ኃይሉ ሻውልን መተካት የለብንም ብሏል፡፡ ድንቄም ለዴሞክራሲ ታግሎ ልቡ ወልቋል፡፡

ለመሆኑ ኃይሉ ሻውልንና መለስ ዜናዊን በየትኛው ሚዛን ላይ አስቀምጦ ይሆን ኃይሉ ሻውል የአማራ ዲታክታር የሆኑት? ለሰዬ አብርሃ መታሰቢያ ባደረገው፣ የግል ዝናውን ባወሳበትና የቆጥ የባጡን በወሻከተበት መጽሐፉ ውስጥ በዴሞክራሲያ መንገድ ተዋቅሮ በሕዝብ የተመረጠው የቅንጅት ፓርቲ ያውም ባልተገኙበት ስብሰባ በፕሬዚዳንትነት መመረጣቸውን እንደዘገበ ከምን ጊዜው ረሳው? ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የመሠረቱትን መኢአድ በመጠጋት ታዋቂነት እንደሚያስገኝ አውቆ አልነበረምን በቅጡ ያልተደራጀውን ምንም ዓይነት የድጋፍ ድርጅት ያልነበረውን ቀስተ ዳመና የተባለውን አናሳ ፓርቲ ይዞ ለመዋሃድ የመጣው? ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል በኢትዮጵያ ሕዝብና በቅንጅት ፓርቲ የተመረጡ፣ የኢትዮጵያን ጥቅም አሳልፈው ለባዕዳን የማይሸጠ ጡ፣ ለፍርፋሪ ሥልጣን እንደ ብርሃኑ ነጋ የማይሞዳሞዱ፣ እንደ ብርሃኑ ነጋ ወያኔ በዘራቸው ምክንያት ከዩኒቨርሲቲ የተባረሩ ፕሮፌሰሮችን ቦታ ለመያዝ የማይስገበገቡ፣ ቆራጥና የመረጣቸውን ሕዝብ አደራ የሚያከብሩ ብርቅዬ ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ ዶተሩ ግን አእምሮው በክህደትና በመናፍቅነት ጭጋግ ስለተሸፈነበት በሕዝብ ተመርጦ መሪ መሆንና በጠመንጃ ኃይል መሪ መሆንን ለመለየት ተስኖታል፡፡ ይህንን መለየት ያልቻለው ዶክተር ለዴሞክራሲ እታገላሁ እያሉ ሲወሻክትላቸው የሚያጨበጭቡለት ታዳሚዎች የማሰብ ችሎታቸው በእጅጉ የተሰናከለ መሆኑን ለመረዳት አያዳክትም፡፡ ግም ለግም አብረህ አዝግም እንላለን፡፡

ሕዝብ መስዋዕትነት የከፈለበትን የነጻነት ትግል ቅንጅት ውስጥ ሰርገው የገቡ ደላላዎች ሲቸበችቡትና ሲያወናብዱበትና ለግል ኑሮ ማደላደያ ሲያደርጉት አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በቸልታ መቷየት የለባቸውም፡፡ ትግሉን የሚሸጡትን ባንዳዎች ማጋለጥ ይጠበቅብናል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸንፋል !